ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies (FSS)

መጋቢት 2003 ዓ.ም. | የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች | ቁጥር 30

# የአየር ንብረት ለውጥና የኑሮ ዋስትና በሰሜን ኢትዮጵያ፤

## ተፅእኖው፣ የገጠሩ ህብረተሰብ ተሞክሮና ለወደፊቱ የማጣጣም ሥራ የሚኖረው አንድምታ

የማኅበራዊ ጥናት መድረክ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ-ነክ ምርምሮችን የሚያደርግ ለትርፍ ያልተቋቋመና መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ነው፡፡

የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል፡፡

በአዲስ አበባ (በ97.1 ሞገድ) እና በአዋሳ (በ100.9 ሞገድ) ከተሞች ኤፍ.ኤም.ራዲዮ ጣቢያዎች ልማት ነክ ጉዳዮችን እያዘጋጀ ያሰራጫል፡፡

በድረ-ገጹ የሕትመት ውጤቶቹን ዝርዝር ያቀርባል፡፡

በርዕሱ ዙሪያ ሐሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜይል አድራሻችን ላኩልን፡፡

## 1. መግቢያ

የአየር ንብረት ለውጥ እየከፋና እየተባባሰ የሚሄድ ዋነኛ የልማትና የዘላቂ ለውጥ ችግር ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአየር ንብረት ላይ ጥገኛ ሆኖ የተመሠረተ ከመሆኑ አንፃር ለወጡ የሚፈጥረው ጫና በእጅጉ ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የአየር ንብረት ለውጥ የሀገሪቱን የወደፊት የዕድገት ደረጃና ህልውና ከሚወስኑ ጉዳዮች በግምባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱት ዋነኛው እንደሚሆን እሙን ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የአየር ንብረት ለውጥ ተፅእኖን ለመቋቋምና ከተተለመው ሀገራዊ የእድገት አቅጣጫና ራዕይ ጋር አጣጥሞ ለማስኬድ የሚያስችል አስፈላጊውን አቅም መፍጠርና ማጠናከር፣ ተገቢውን የቅድመ ዝግጅት ስራ በተገቢው መከወንና ለትግበራ መንቀሳቀስ እንደ አማራጭ የሚወሰድ ሳይሆን እንደ ዋነኛ ስልት ሆኖ መወሰድ ያለበት ጉዳይ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ለዚህም ዐብይ ዓላማ ለአየር ንብረት ለውጥና የተፈጥሮ አደጋዎች ይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑ የኢኮኖሚ አውታሮችና የማህበረሰብ ክፍሎች ልዩ ትኩረት በማድረግ በጥናትና ምርምር የታገዘ የአየር ንብረት ለውጥ የማጣጣሚያ መርሐ-ግብር ዘርግቶ ለትግበራና አፈፃፀም ተግቶ መንቀሳቀስ የግድ ይሆናል፡፡

አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፎች የአየር ንብረት ለውጥን ተከትሎ ለሚከሰቱ የተለያዩ አደጋዎችና ፈርጀ-ብዙ ተፅእኖዎች የተጋለጡ ናቸው፡፡ በተለይ የተፈጥሮ ሀብታቸው በእጅጉ በተመናመነ አካባቢዎች የሚኖሩ በግብርና የሚተዳደሩ አነስተኛና ድሀ ሴትና ወንድ ገበሬዎች የአየር ንብረት ለውጥ ለሚፈጥራቸው አደጋዎችና ተፅእኖዎች በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ ሲሆኑ በሚኖሩባቸው የገጠር አካባቢዎች ያለው የተንሰራፋ የድህነት መጠንና ውሱን የኢኮኖሚና ማህበራዊ አገልግሎት ደረጃ አደጋውን የከፋና የህብረተሰቡን ዝግጁነትና የመቋቋም አቅም ደካማ አድርገውታል፡፡ ይህንኑ ጉዳይ በመገንዘብ የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ ቀደም ሲል የአየር ንብረት ለውጥ አደጋዎችን፣ ተፅእኖዎችንና ምላሻቸውን በተመለከተ ሁለት አመት የፈጀ የዳሰሳ ጥናት በተመረጡ የደቡብ ኢትዮጵያ የአርብቶ አደር አካባቢዎች አከናውኖ የጥናቱን ውጤት ለሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት ማሰራጨቱ ይታወሳል፡፡ ይህኛው ጥናት የዛ ጥናት ተከታይ ሆኖ በድርጅቱ ባለሙያ አማካይነት በተመረጡ የሰሜን ኢትዮጵያ የገጠር ወረዳዎችና ቀበሌዎች የተከናወነ ሲሆን የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶችና የፖ`ሊሲ መወያያ ነጥቦች እንደሚከተለው ባጭሩ ቀርበዋል፡፡

## 2. የጥናቱ ዓላማና የተጠቀመባቸው ዘዴዎች


የጥናቱ ዋና የትኩረት አቅጣጫ የአየር ንብረት ለውጥን ተከትለው ለሚከሰቱ የተለያዩ አደጋዎች፣ አደጋዎቹ የሚፈጥሯቸውን ፈርጀ-ብዙ ተፅእኖዎችና በህብረተሰቡና በልማት አጋሮች ያሉ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ መልካምና አዳዲስ የሚባሉ ጠቃሚ ልምዶችንና ተሞክሮዎችን በመዳሰስ ለሚመለከ ታቸው አካላት የጉዳዩን አሳሳቢነትና የመፍትሄ ሃሳቦችን የሚጠቁም የፖ`ሊሲ ፍሬ ሀሳብ ማመንጨት ነው፡፡

ጥናቱ የተካሄደው በሰሜን ኢትዮጵያ ለናሙና በተመረጡ የሰሜን ወሎ እና የደቡባዊ ትግራይ ሁለት ወረዳዎችና አራት የገጠር ቀበሌዎች ነው፡፡ ጥናቱን ለማካሄድ የተለያዩ የጥናትና የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን ለመጠቀም ተሞክሯል፡፡ ከቤተሰብ ተኮር ጥልቅ የመረጃ ማሰባሰቢያ መጠይቅ ጀምሮ የአንድ ለአንድና የቡድን ጥልቅ ውይይቶችንና ጥናቱ ባተኮረባቸው አካባቢዎች ከሚገኙ የዞን፣ የወረዳና የቀበሌ የአስተዳደር አካላትና የሴክተር መስሪያ ቤቶች እንዲሁም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጽ/ቤት ሐላፊዎችና ተጠሪዎች ጋር ጠቃሚ ውይይቶች ተካሄደዋል፡፡ በተጨማሪም የባለሙያ አስተያየቶችን፣ቀጥታ የመስክ ምልከ ታዎችንና የፎቶግራፍ ምስሎችን ለመጠቀምና የአካባቢውን የ30 አመት የዝናብ መጠንና ስርጭት እንዲሁም የሙቀቱን ሁኔታ በመተን ተን የአየር ንብረት ለውጡን ለመጠቆም ተሞክሯል፡፡


## 3. የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች

### *3.1 የአየር ንብረት ለውጥ መገለጫዎችን በተመለከተ*

ጥናቱ የተካሄደባቸው የሰሜን ወሎ እና የደቡባዊ ትግራይ ወረዳዎችና የገጠር ቀበሌዎች (ጣቢያዎች) ታሪክ በአብዛኛው ከድርቅ፣ ከርሀብና ከተፈጥሮ ሀብት መመናመን ጋር በእጅጉ የተቆራኘ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከዚህ አንፃር በአካባቢው ዝቅተኛና በእጅጉ የሚዋዥቅና አስተማማኝ ያልሆነ የዝናብ መጠንና የተዛባ ስርጭት እንዲሁም ከፍተኛና የመጨመር አዝማሚያ የሚያሳይ የሙቀት ሁኔታ ይታይባቸዋል፡፡ በአካባቢው አማካይ አመታዊ የዝናቡ መጠን ከ400-800 ሚ.ሜ ሲሆን የሙቀት መጠኑም በአማካይ 23°C ነበር፡፡




አማካይ የሙቀት ሁኔታ በራያ አዘቦ




አማካይ አመታዊው የዝናብ መጠን በመቀት

ከህብረተሰቡ እና ከብሔራዊ ሜቴዎሮሎጂ በተሰበሰበው መረጃ (ከላይ በስዕላዊ መግለጫው እንደተመለከተውም) ላለፉት 30 አመታት የሙቀት መጠኑ በሁሉም አካባቢዎች እየጨመረ የመጣ ሲሆን የዝናቡ ሁኔታም በከፍተኛ ሁኔታ መዋዥቅና በመጠኑም ቢሆን የመቀነስ አዝማሚያ አሳይቷል፡፡ ከህብረተሰቡና ከባለሙያዎች ከተሰበሰበው መረጃ ለመረዳት እንደተቻለውም የዝናቡ ሁኔታ በመጠን እየቀነሰ፣ በስርጭቱና በአዘናነብ ባህሪው ወቅቱን ያልጠበቀ መሆኑንና በጣም ከመዛባቱ የተነሳ ለመተንበይ የሚያዳግት እየሆነ እንደመጣ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በአካባቢው ከሙቀት መጨመር ጋር በተያያዘ ከሚፈጠር ከፍተኛ የፀሐይ ግለትና የነፋስ ድግግሞሽ ጋር ተደምሮ የተራዘመ የድርቅ ወራት እንዲኖር ምክንያት እየሆነ መምጣቱን ለመገንዘብ የተቻለ ሲሆን በሌላ በኩል አልፎ አልፎም ቢሆን ሳይጠበቅ የሚጥል ከመጠን ያለፈ ዝናብ የመከሰቱ ሁኔታ እየጨመረ መጥቷል፡፡ በመቀትና በራያ አዘቦ ወረዳዎች ከተሰበሰበው የቤተሰብ መጠይቅ እንደተመለከተው በአካባቢው ከ90% በላይ የሚሆኑት አባወራዎችና እማወራዎች የአየር ንብረት ለውጥ አዝማሚያ የታዘቡ መሆናቸውን መስክረው ለዚህም መገለጫው የሙቀት መጨመር፣ የዝናብ መጠን መቀነስ፣ የዝናቡ ቀናት ማሽቆልቆል፣ የዝናቡ ስርጭቱ በእጅጉ መዛባትና ከሚጠበቅበት ወቅትም በእጅጉ ቀድሞ ወይም ዘግይቶ የሚመጣና የሚሄድ መሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም የክረምቱ ወራት ቅጥ አልባ መሆንና መዘበራረቅ መታዘባቸውን ገልፀዋል፡፡

## *3.2 የአየር ንብረት ለውጥ ያስከተላቸው አደጋዎች ተፅእኖዎች*

### 3.2.1 በገጠር የቤተሰብ ኑሮ ዋስትና ላይ ያስከተለው ተፅእኖ በእንስሳት ሀብት ይዞታ ላይ የደረሰ ተፅእኖ

የናሙና ጥናቱ በተካሄደባቸው የመቀትና የራያ አዘቦ ወረዳዎች ለድህነት መስፋፋት፣ ለቤተሰባዊ ሀብት መዳሸቅ፣ የምግብ ዋስትና እጦትና ለተፈጥሮ ሀብት መመናመን (በተለይ የአፈር መከላትና ለምነት ማጣት፣ የውሃና የግጦሽ ሀብት መመናመን፣ የሰብል ምርት መቀነስና አልፎ አልፎም ቢሆን ጨርሶ መጥፋትና የእንስሳት ሀብት ምርትና ምርታማነት መቀነስ) የአየር ንብረት ለውጥ ተጠቃሽ ምክንያት ነው፡፡ በተለይም ባለፉት 20 አመታት (ከ1990-2010 እ.ኤ.አ) በተደጋጋሚ በተከሰተና ለረዥም ወራት በቆየ የድርቅ አደጋ፣ አልፎ አልፎ በተከሰተ ያልተጠበቀ የጐርፍ አደጋና የእንስሳትና የሰብል በሽታ ሰበብ የሰብል እና የእንስሳት ሀብት ምርትና ምርታማነት ማሽቆልቆል በድሀ የገበሬ ቤተሰቦች ላይ የሀብት መዳሸቅንና የኑሮ ዋስትና መናጋትን አስከትሏል፡፡ ለምሳሌ ለናሙና በተመረጡት የገጠር ቀበሌዎች የእንስሳት ሀብት ይዞታ በአማካኝ በመቀት ወረዳ ከ2.4 በሬ ወደ 0.3፣ ከ3 ላሞች ወደ 0.5፣ ከ7 በግና ፍየሎች ወደ 2 ያሽቆለቆለ ሲሆን በተመሳሳይ ጥናቱ በተካሄደባቸው የራያ አዘቦ ሁለት የገጠር ቀበሌዎች (ሐውልቲ እና አደ-ሐሊጋ) እንዲሁ አማካይ የቤተሰብ የእንስሳት ሀብት መጠን ከ3 በሬ ወደ 0.5፣ ከ3 ላሞች ወደ 0.7፣ ከ10 በግና ፍየሎች ወደ 4 አሽቆልቁሏል፡፡

**በሰብል ምርትና በቤተሰብ የምግብ ዋስትና ላይ የደረሰ ተፅእኖ**

ባለፉት ጥቂት አመታት በተከታታይ በተከሰተ የድርቅ፣ የውርጭ፣ የጐርፍና የሰብል በሽታ ምክንያት በመቀትና ራያ አዘቦ ወረዳዎች በሚገኙ ጥናቱ በተካሄደባቸው ቀበሌዎች ብዙ ቤተሰቦች ለምግብ ዋስትና እጦት ተጋልጠው ነበር፡፡ ለምሳሌ በመኸር 2002 ዓ.ም በድርቅ፣ በውርጭና በሰብል አጥፊ ተህዋስያንና ፍጥረታት ሰበብ በመቀት ወረዳ ብቻ ከ41,000 በላይ ቤተሰቦች በምግብ ዋስትና እጦት ተጠቅተዋል፡፡ በመስክ ላይ በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ወደ 80% የሚጠጉት ቤተሰቦች ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ በተከሰተ ተደጋጋሚና የተራዘመ የድርቅ አደጋ፣ ያልተጠበቀ የውርጭና የበረዶ ክስተት፣ ያልተጠበቀ የጐርፍ አደጋና የሰብል ተባይ ምክንያት የሰብል ምርትና የውሃ አቅርቦት ላይ ጫና ተፈጥሯል፣ የምግብ ዋስትና ችግርም ተባብሷል ብለዋል፡፡





የአየር ንብረት ለውጥ የአፈር መከላትን ያባብሳል፤በሰብል ምርትና ምርታማነት ላይም ጫና ያደርጋል

### 3.2.2 በጤና ዘርፍ እና በማህበራዊ ሕይወት/ትስስር ላይ የተፈጠረ ተፅእኖ

የአየር ንብረት ለውጥ የሙቀት፣ የዝናብና የነፋስ ሁኔታዎችን በመለዋወጥና እንደ ድርቅ፣ ጐርፍ፣ ውርጭ፣ ብርድ የመሳሰሉ አደጋዎችን በመፍጠርና በማባባስ፣ ለበሽታ አምጭ ተህዋስያንና የሰብል ተባይ አመች የመራቢያ ሁኔታዎችን በመፍጠር በጤና ላይ ቀጥተኛ የሆነ ተፅእኖ ወይም ሳንካ ከመፍጠር ባሻገር በተዘዋዋሪ መንገድ የምግብና የውሃ እጥረትንና የአካባቢ መጉሳቆልን በማባባስ ለተለያዩ የምግብ፣ የውሃና የባክቴሪያ ወለድ በሽታዎች ይዳረጋል፡፡ ጥናቱ በተካሄደባቸው የገጠር ቀበሌዎች ከተሰበሰበው የፅሁፍና የቃል ማስረጃ ለማረጋገጥ እንደተቻለው ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ በአካባቢዎቹ ከወባ መስፋፋት (ቀደም ሲል ከሚታወቅባቸው ቆላማና ከፊል ቆላማ የገጠር ቀበሌዎች ወደ ደጋማ አካባቢዎች የመከሰትና የመስፋፋት ሁኔታ) በተጨማሪ እንደ ተቅማጥ፣የትንፋሽና የውስጥ (የመተንፈሻ) አካላት በሽታዎች መከሰትና መስፋፋት ታይቷል፣ የእንስሳት በሽታና የሰብል ተባይ ክስተትም እንዲሁ መስፋፋት ታይቷል፡፡ ለምሳሌ በራያ አዘቦ ወረዳ በ2000 እና በ2001 ዓ.ም በአጠቃላይ ከወረዳው ህዝብ 34,464 የሚሆነው በወባ ተጠቅቶ እንደነበር በወረዳው ጤና ጽ/ቤት ሲመለከት በመቀት ወረዳም በተመሳሳይ በ1998 ዓ.ም እና በ2001 ዓ.ም

9,690 ሰዎች በወባ ተጠቅተው ነበር። ከዚህ በተጨማሪ በተደጋጋሚ ድርቅ፣ውርጭ፣ጐርፍና ብርድ ምክንያት በተፈጠረ የሰብልና የእንስሳት ምርትና ምርታማነት ማሽቆልቆልና የቤተሰብ ሀብት መዳሸቅ ሰበብ ቀደም ሲል ለድህው የገጠር ቤተሰብ እንደዋስትና ያገለግሉ የነበሩ ባህላዊ የመረዳዳትና የመተዛዘን ሆኔታዎች እየተዳከሙና ባህላዊ ትስስሩም እየላላ መምጣቱን ለመገንዘብ ተችሏል።

### 3.2.3 በብዝሃ ሕይወትና በሥነ-ምሕዳር ላይ የታዩ ተፅእኖዎች

ጥናቱ በተካሄደባቸው አካባቢዎች ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ በሚከሰት ተደጋጋሚና የተራዘመ የድርቅ አደጋና ያልተጠበቀ የጐርፍ ክስተት በጊዜ ሂደት የምድርና የከርሰ ምድር ውሃ መጠን፤ የደንና የግጦሽ ሀብት መመናመን እንዲሁም የበረሃማነት መስፋፋት ተከስቷል። በአንዳንድ መንደሮች ነዋሪዎች እንደመሰከሩት አንዳንድ ኩሬዎችና አነስተኛ ጅረቶች የደረቁ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ መጠናቸው ቀንሶ ወቅታዊ ሆነዋል። በተለይ በመቄት በተደጋጋሚ ድርቅ፣ ውርጭና በረድ ምክንያት የአፈር ድርቀትና መፍረክረክ የሚከሰት ሲሆን አንዳንድ ጊዜ በሚከሰት ከመጠን ያለፈ ድንገተኛ ዝናብ ሰበብ ከፍተኛ የሆነ የአፈር መከላት ስለሚከሰት በግብርና ምርት፣ በብዝሃ ህይወት እና በሥነ-ምህዳር ላይ የሚታዩ ተፅእኖዎች ቀላል የሚባሉ አይደሉም። ከዚህ አንፃር በጥናቱ ከተካተቱት የገበሬ ቤተሰቦች በአማካይ በመቄት ከ80% በላይ የሚሆኑት በራያ አዘቦ ደግሞ ወደ 41% የሚጠጉት በአየር ንብረት ለውጥ ሰበብ በየቀበሌአቸው የተፈጥሮ ሀብት (በተለይም የአፈር፣ የውሃና የደን) መመናመን መድረሱን መታዘባቸውን ገልፀዋል።

## 4. በተለይ ተጠቂ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች

የአየር ንብረት ለውጥ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ሊያጠቃ የሚችል መሆኑ ቢታወቅም በጥናቱ ለማረጋገጥ እንደተቻለው በከፍተኛ የድህነት አረንቋ የሚኖሩ መሬት፣ የቤት እንስሳት ወይም ጠቃሚ ንብረትና ተጨማሪ የገቢ ምንጭ የሌላቸው በእማውራ የሚመሩ፤ ባለብዙ ጥገኛ ቤተሰብ የሆኑና በአነስተኛ ማሳ እና ጊዜያዊ በሆኑና በማያስተማምኑ በጥቃቅን የገጠር ስራዎች የሚተዳደሩ ድሃ ቤተሰቦች በእጅጉ ተጋላጭ መሆናቸው ታውቋል። አነስተኛ የሚባሉ የአየር ንብረትና የተፈጥሮ አደጋዎችን እንኳን ለመቋቋምና ለወደፊቱም ያላቸው ዝግጁነት በእጅጉ ደካማ በመሆኑ ከፍተኛ ድጋፍ የሚሹ ናቸው።

## 5. የአየር ንብረት ለውጥና የገጠር ሴቶች ሁኔታ


ጥናቱ በተካሄደባቸው የገጠር ቀበሌዎች የሚኖሩ ሴቶች በአካባቢ ጥበቃ፣ በቤተሰብ ኢኮኖሚና በዘላቂ ልማት ትግበራ እንቅስቃሴዎች ላይ ያላቸው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው። ሆኖም ካለባቸው የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና፣ የሥራ ይዘትና በተለይም እማዎራዎችና ድህነት በተንሰራፋባቸውና ብዛት ያላቸው የቤተሰብ አባላት በሚኖሩበት ቤተሰብ የሚኖሩ ሴቶች ካለባቸው የቤተሰብና የኢኮኖሚ ጫና በተጨማሪ ከተፈጥሮ ሀብት ጋር የኑሮ ዋስትናቸው በየዕለቱ በመቆራኘቱ የአየር ንብረት ለውጥ ለሚያመጣው ጫና በከፍተኛ ሁኔታ ተጋላጭ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል። ለአስረጅነት ያልተራዘመ የድርቅ ወራትን ተከትሎ በሚከሰት የውሃና የማገዶ ችግር ምክንያት ጥናቱ በተካሄደባቸው የመቄት ቀበሌዎች የሚኖሩ ሴቶች በአማካይ ውሃ ለመቅዳት 10 ኪ.ሜ ያህል እንዲሁም የማገዶ እንጨት ለመልቀም ከ16 ኪ.ሜ በላይ ለመገንዝ የሚገደዱ ሲሆን በተመሳሳይ በራያ አዘቦ ቀበሌዎች ውሃ ለመቅዳት እስከ 7 ኪ.ሜ እንዲሁም ማገዶ ፍለጋ እስከ 13 ኪ.ሜ ለመጓዝ የሚገደዱበት ወቅት ይኖራል። በአጠቃላይ ጥናቱ በተካሄደባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ ሴቶች በአማካይ በቀን ከ14-17 ሰዓት የሚሰሩ ሲሆን ይህ የስራ ሰዓትም በድርቅና በችጋር ወራት በቀን በአማካይ ከ16-18 ሰዓት የሚደርስበት ሁኔታም እንዳለ በጥናቱ ተረጋግጧል። በአጠቃላይ በአየር ንብረት ለውጥ ሰበብ በሚከሰት የምግብና የውሃ እጥረት፣የማገዶ ችግር፣ የእንስሳት መኖ መመናመን እንዲሁም የባህላዊ መድሃኒቶችና በተለይ ለችግረኛ ቤተሰቦች በክፉ ወራት የምግብ ምንጭ የሆኑ የዛፍና የፍራፍሬ ዝርያዎች መጥፋት በድሃ የገጠር ሴቶች ላይ ከፍተኛ የኑሮና የስራ ጫና በመፍጠር ለከፋ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ሲዳርጓቸው ተስተውሏል።


## 6. የአየር ንብረት ለውጥ ለሚፈጥራቸው ተፅእኖዎች አባባሽ ምክንያቶች


ጥናቱ በተካሄደባቸው የመቄት ቀበሌዎች የሚኖሩ በእርሻና በጥቃቅን ግብርና ነክ ሙያዎች የሚተዳደሩ ድሃ የገጠር ቤተሰቦች ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ ከሚፈጠርባቸው ተፅእኖ በተጨማሪ የተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች መኖር ተፅእኖውን የመቋቋም አቅማቸውን እንደሚያዳክ ምባቸው በጥናቱ ተረጋግጧል። ከእነዚህም መካከል ክፉኛ የአፈር መበላትና የመሬት መጐሳቆል፣የተፈጥሮ ሀብት መመና መን፣ ስደት (distress migration)፣ ከገበያ፣ ከመረጃና ከሌሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የአገልግሎት ዘርፎች ርቆ መገኘት፣ ደካማ የሆነ የቅድመ ማስጠንቀቂያና የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት አገልግሎት እንዲሁም ከፍተኛ የሆነ የህዝብ እድገት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

## 7. የአየር ንብረትን ለመቋቋም የህብረተሰቡ ዝግጁነትና ምላሽ

ይህ ጥናት በተካሄደባቸው የመቄትና የራያ አዘቦ የገጠር ቀበሌዎች የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች አካባቢያቸውንና ዋነኛ መተዳደሪያ የሆናቸውን የግብርና ሙያ በተመለከተ ለዘመናት የካበተ እውቀት፣ ልምድና ክህሎት ስላላቸው አስደናቂ ሊባሉ የሚችሉ የሰብል አመራረት፣ የእንስሳት አያያዝና የተፈጥሮ ሀብትና እንክብካቤ ዘዴዎችን በመጠቀም አስቸጋሪና ፈታኝ ከሆነው የመሬት አቀማመጥ፣ የተፈጥሮ ሀብትና የአየር ንብረት ሁኔታ የተሻለና የተረጋጋ ኑሮን ለመምራት ለዘመናት ጥረዋል። ከቅርብ ዓመታት ወዲህም ቢሆን የአየር ንብረት ለውጥ የሚፈጥራቸውን ተጨማሪ ስጋቶችና አደጋዎችን ለመቀነስና ተፅእኖዎቹን ለመቋቋም ተጨማሪና አዳዲስ ወይም የተሻሻሉ የሰብል አመራረት፣ የመስኖ አጠቃቀም፣ የአፈርና ውሃ አያያዝና አጠቃቀም፣ ጥምር የግብርና እና የደን ሀብት ልማት፣ የእንስሳት መኖ ልማትና አጠቃቀም፣ የእንስሳት ሀብት አረባብ ዘዴዎችንና ተጨማሪ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የችግር መቋቋሚያና የኑሮ መደጐሚያ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። ይሁን እንጂ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የአየር ንብረት ለውጥ የሚፈጥራቸው አደጋዎችና ተፅእኖዎች እየበዙና እየተባባሱ በመምጣታቸው አብዛኛዎቹ ባህላዊ የችግር መቋቋሚያና ማስወገጃ ዘዴዎች እየተዳከሙ፣ የውጤታማነትና የዘላቂነት ደረጃቸውም አጠያያቂ እየሆነ መጥቷል። ሥለሆነም ህብረተ ሰቡ የአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተጣጥሞ ለመኖር ከፍተኛ የሆነ የውጭ ድጋፍ ይሻል።







የውሃ እቀባ ፣ የአፈርና ተፈጥሮ ሐብት ጥበቃ ወሳኝ ነዉ

## 8. መንግስታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት እገዛና ምላሽ

መንግሥታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ የልማት ተቋማትና ድርጅቶች በአካባቢው ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን አደጋዎች ስጋት ለመቀነስና ተፅእኖዎቹንም ለመቋቋም የሚያግዙ የተለያዩ የአቅም ግምባታ፣ የመሰረተ ልማት ግምባታ፣ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና በአደጋ ጊዜ የአስቸኳይ የእርዳታ ማሰባሰብ ስራዎችን ይሰራሉ፡፡ በተለይ ጥናቱ በተካሄደባቸው የራያ አዘቦ የገጠር ቀበሌዎች በወረዳው የግብርና ቢሮ (የክልሉ መንግስት) እና በማህበረ ረድኤት ትግራይ ትብብር በተፈጥሮ ሀብት ልማት፣ በቤተሰብ ጤና እና የገቢ ማዳበሪያና ማስፋፊያ እንዲሁም በመሠረተ ልማት ግምባታ በኩል እየተሠራ ያለው ስራ እንዲሁም በግብርናው ዘርፍ እየተሞከሩ ያሉ አዳዲስ የሰብልና የፍራፍሬ ዝርያዎችና አሠራሮች ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ህብረተሰብና ኢኮኖሚ ከመገንባት አንፃር የሚኖራቸው ፋይዳ ቀላል አይደለም፡፡

ሆኖም በአንዳንድ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በኩል በተወሰነ መልኩ በቦታ፣ በጊዜና በአቅም የተወሰኑ አሳታፊነትና ዘላቂነት የሚጐላቸው ለየብቻ የሚተገበሩ የልማት ስራዎች መስተዋላቸው እንደ ዋነኛ ችግር የሚጠቀስ ሲሆን በመንግስት ተቋማት በኩልም ቢሆን የሚሠሩ የልማትና የአቅም ግምባታ ስራዎች በአብዛኛው በአካባቢው ህብረተሰብ ሙሉ ፍላጎትና ተሳትፎ በመመስረት በዘላቂነትና በወጥነት የረዥም ጊዜ ግቦችን ከማሳካትና የአደጋ ስጋቶችን ከመቀነስ ይልቅ የአጭር ጊዜ የኢኮኖሚ ግቦችን ከማሳካትና የአደጋ ጊዜ ዕርዳታዎችን በማስተባበር ያተኮሩ በመሆናቸው የአየር ንብረት ለውጥ ተፅእኖን ለመቋቋም አስፈላጊውን የአካባቢያዊ አቅምን ከማጐልበት አንፃር ብዙ የሚቀራቸው መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

## 9. ከጥናቱ የተገኙ ጠቃሚ ትምህርቶችና ልምዶች

በጥናቱ ወቅት ከአየር ንብረት ለውጥ ቀጥተኛ ተጠቂ ከሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችና እነርሱን በሙያቸው ከሚያግዙ ባለሙያዎች ጋር በተደረጉ ጠቃሚ ውይይቶችና የመስክ ምልከታዎች ለወደፊቱ በተቋማት በኩል ለሚደረጉ የተለያዩ የልማትና የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ስራዎች የሚጠቅሙ ትምህርቶችንና ተሞክሮዎችን ለማሰባሰብ ተችሏል፡፡ ከእነዚህም መካከል ከማንኛውም የልማትና የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ መርሐ-ግብር ዝግጅትና ትግበራ በፊት የአካባቢውን የኑሮ ዋስትና እና ዋና ዋና የገቢ ማስገኛ ስራዎችን መለየትና ተጋላጭነታቸውን በተገቢው መፈተሽ፣ በአካባቢው ያለውን ለአየር ንብረት ተጋላጭነት፣ ዋና ዋና የአየር ንብረት ለውጥ አደጋዎችን፣ በይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችንና የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎችን በተገቢው መለየት፣ በአየር ንብረት ለውጥ መነፀርነት በአካባቢው ያሉ የተለያዩ (ጠቃሚ፣ ጐጅ ወይም አዳዲስ) የሚባሉ ልምዶችንና አሠራሮችን ጠንቅቆ መረዳት፣ የአካባቢው ህብረተሰብን (በተለይም የሴቶችንና ሌሎች ይበልጥ ተጐጂና ተጠቂ የሆኑ ክፍሎችን) ሙሉ ተጠቃሚነትና ተሳትፎ ማረጋገጥና ፣ ከአስተቃቀድ ወቅት ጀምሮ እስከ ትግበራና የአፈፃፀም ግምገማ ድረስ የሁሉንም የባለድርሻ አካላት ተሳትፎና ይሁንታ ማረጋገጥ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

## 10. የፖሊሲ መወያያ ሐሳቦች

- የአየር ንብረት ለውጥ ለህልውናችንም ሆነ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገታችን ትልቁ ፈተና መሆኑ በ5 ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ መታመኑና ዕውቅና መስጠቱ ትልቅ ስኬት ነው፡፡ ሆኖም ይህንን ዕውቅና ስንሰጥ በአጠቃላይ በሀገሪቱ ዕቅዱን ለማስፈፀም የሚዘጋጁ ወይም የሚወሰዱ እርምጃዎች ይህንኑ ሀቅ መንተራስና ተገቢውን ትኩረት የሰጡ መሆናቸውንና ለማጣጣም የሚደረጉ ጥረቶች በሙሉ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ማህበረሰብንና ኢኮኖሚን ከመገንባት አንፃር መቃኘት ይኖርባቸዋል፡፡

- የአየር ንብረት ለውጥ የማጣጣሚያ መርሐ-ግብሮችንና የመፍትሄ እምርጃዎችን ከድህነት ቅነሳ፣ ከምግብ ዋስትና እና ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ስራዎች ጋር አዋህዶና አቀናጅቶ በየአካባቢው ማህበረሰቦች የሚገኙ ጠቃሚ ልምዶችና እውቀቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለተግባራዊነቱ በቅንጅት መንቀሳቀስ ጥቅሙና ዘላቂነቱ የጎላ ይሆናል፡፡

- የሰብዓዊ ልማትና የማህበራዊ ጥሪት (social capital) ግምባታ የድሃ ቤተሰቦችን፣ የሴቶችንና ሌሎች በተለይ ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ አካላትን አቅም ያጎለብታል፡፡

- ብዝሃ ሕይወትንና ሥነ-ምህዳርን መሠረት ያደረገና ዘላቂነት ያለው የተፈጥሮ ሀብት አያያዝና (በተለይ የመሬት፣ የውሃና የሃይል) አጠቃቀምን መተግበር፡፡

- ለአየር ንብረት ለውጥ አደጋዎች ተጋላጭነትን ለመቀነስና ተገቢውን የአካባቢ አቅም ለመገንባት የተለያዩ የመረጃ ማሰባሰብ፣ አያያዝና አጠቃቀም (ስርጭት) ዘዴዎችን፣ የአቅም ግምባታ፣ የመሠረተ ልማትና አማራጭ የስራ ዘይቤዎችን መፍጠርና ማስተዋወቅ ይገባል፡፡

- በሀገሪቱ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ማህበረሰብና ኢኮኖሚን ለመገንባትና የተለያዩ ከካርቦን ሱስ የፀዱ የልማት ስራዎችን ለማከናወን የሚያግዝ የቴክኒክ፣ የገንዘብና የተስማሚ ቴክኖሎጂ ድጋፍ ለማሰባሰብ በተቀናጀና ቀጣይነት ባለው መልኩ ተግቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡

**አቶ አለባቸው አደም**

__ምንጭ__፡- ***Alebachew Adem***. 2010. *Climate change and rural livelihoods in northern Ethiopia: Impacts, poor peoples' adaptation experiences and the implications for instuitutional interventions*. *A* study commissioned by Forum for Social Studies (FSS), Addis Ababa.

__ምስጋናና ማሳሰቢያ__

ይህ ሰነድ የታተመው በለጋሾች ቡድን የገንዘብ ድጋፍ ነው፡፡ ለሰነዱ ይዘት ሙሉ ኃላፊነቱ የደራሲው ሲሆን በምንም ሁኔታ የለጋሾች ቡድንን ወይም የአሳታሚውን አቋም እንደሚያንፀባርቅ ተደርጐ መወሰድ የለበትም፡፡

አድራሻ፡- ፎረም ፎር ሶሻልስተዲስ፣ ፖ.ሳ.ቁ 25864 ኮድ 1000 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
❄ **ስልክ** 011-629 78 88/91 ❄ **ፋክስ** 011-629 78 89 ❄ **ኢሜይል:** fss@ethionet.et ❄ **ድረ-ገፅ** www.fssethiopia.org.et